
እምነትን መያዝ
ትምህርት 8 ለ ግንቦት 15፣ 2018



“እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።”

(ዕብራውያን 11:1)


እግዚአብሔርን ማወቅ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና ጸሎት በህይወታችን ውስጥ ለውጥ አምጪ እንዲሆኑ አንድ የጋራ ግብአት ያስፈልጋቸዋል፤ እርሱም እምነት ነው።



ያለ እምነት እነዚህ ተግባሮች እውቀት ብቻ ወይም ትርጉም የሌላቸው ስርዓቶች ብቻ ይሆናሉ።

ነገር ግን ከእምነት ጋራ እነዚህ በመንፈሳዊ ልምምዳችን ወደ ከፍታ ጫፍ ላይ የሚወስዱን ኃይለኛ መሳሪያዎች ናቸው። "…ለሚያምን ሁሉ ይቻላል" (ማር 9:23)።





**ልዩ ልዩ የእምነት አይነቶች:**

- እምነት እና ምልክቶች
- የእምነት መጠን
- እምነት እና ስሜቶች

**እምነት ምንድን ነው?**

- የእምነት ምንነት እና እድገት
- የኢየሱስ እምነት

# ልዩ ልዩ የእምነት አይነቶች

# እምነት እና ምልክቶች

"ስለዚህም ኢየሱስ፦ ምልክትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ ከቶ አታምኑም አለው።" (ዮሐንስ 4:48)







ምልክት ማለት አንድን ከመለኮት የመጣ መልዕክትን ወይም ስልጣንን ለማረጋገጥ የሚሰጥ መለያ ወይም ማስረጃ ነው። ምንም እንኳን ምልክት አብዛኛውን ጊዜ፣ ልክ በገሊላ ቃና (ዮሐ 2:11) እንደነበረው፣ ተዓምራዊ ክስተት እንደሆነ ቢታወቅም፣ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ በሲና ተራራ ፊት መስፋራቸውም እንደ ምልክት መሰጠቱን እናስተውላለን (ዘጸ 3:12)።

ፈሪሳውያንም በአንድ ወቅት ኢየሱስ መሲህ መሆኑን አይተው ያምኑ ዘንድ አንድን ምልክት እንዲያሳያቸው ጠይቀውት ነበር (ማር 8:11)



ኢየሱስ እነርሱ የእምነታቸውን ማነስ ለመሸፈን ምልክትን በመጠየቃቸው እጅግ አዝኖ ነበር (ማር 8:12)። ምክንያቱም አንድ ሰው ማመን ካልፈለገ ምንም አይነት ምልክት ሊያሳምነው አይችልም።

እግዚአብሔር ማመን የሚፈልግ ሁሉ እንዲያምን በቃሉና በተፈጥሮ ውስጥ በቂ ማስረጃን ሰጥቶናል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ለጥርጣሬ በሩ ክፍት ነው። ኢየሱስ ሳያይዩ ለሚያምኑ የተለየ በረከትን የሚሰጠውም ለዚህ ነው "ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው" (ዮሐ 20:29)።

# የእምነት መጠን



“ጌታም አለ፦ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ሾላ፦ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተተከል ብትሉት፥ ይታዘዝላችሁ ነበር።” (ሉቃስ 17:6)

**የተለያዩ የእምነት መጠኖች አሉ:**

### የሐዋርያት እምነት




“እንዴትስ እምነት የላችሁም?” (ማር 4:40)

### የጴጥሮስ እምነት



“አንተ እምነት የጎደለህ!” (ማቴ 14:31)

### የዚያ አባት እምነት



“አለማመኔን እርዳው” (ማር 9:24)

### የከነዓናዊቷ ሴት እምነት



“እምነትሽ ታላቅ ነው” (ማቴ 15:28)

### የመቶ አለቃው እምነት



“በእስራኤልስ እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም” (ሉቃ 7:9)

### የእስጢፋኖስ እምነት



“እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው” (የሐዋ 6:5)

የአለማመን ስሮች እየተቆረጡ ሲሄዱ እምነት እያደገ እንደሚሄድ ግልጽ ነው። እምነት በሂደት ጥርጣሬን ሊያስወግድ ይገባል። የሁልጊዜ ጥያቄያችን ሊሆን የሚገባው “እምነት ጨምርልን” ነው(ሉቃ 17:5)።

በመንፈስ ቅዱስ ሥራ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ሕብረት እምነታችን ሲያድግ እናያለን (2ተሰ 1:3)።





# እምነት እና ስሜቶች

"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤"
(ኤፌሶን 2:8)





**እምነት ስሜት ነው ወይስ ምክንያታዊ ድርጊት ነው?**

የዚህ ጥያቄ መልስ እጅግ ወሳኝ ነው። "እንደዳንኩኝ ይሰማኛል" ብሎ ማለትና "እንደዳንኩኝ እርግጠኛ ነኝ" ማለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

እስኪ ከጥንስሱ እንጀምር። የእምነት ምንጭ ከየት ነው? እምነት ከእግዚአብሔር የሚመጣ እና ለእኛ እንደ ስጦታ የሚሰጠን ነው (ሮሜ 12:3 ኤፌ 2:8)።


ለዚህ ስጦታ አዎንታዊ ምላሽን ስንሰጥና እምነትን መለማመድ ስንጀምር ይህ እምነት እንደ ሐሴት፣ እርካታ፣ መንፈሳዊ እረፍት እና የመሳሰሉትን ስሜቶች በውስጣችን ይፈጥርልናል።



ነገር ግን እምነት እራሱ ስሜት ሳይሆን "እርግጠኝነት" እና "መቀበል" ነው (ዕብ 11:1)። በእኛ ጊዜያዊ ስሜት ላይ የተመሰረተ አይደለም። ደካማ እንደሆንን ሲሰማን ወይም መዳናችን የራቀን ሲመስለን እምነታችንን በይበልጥ ልንለማመድ የሚገባን ያን ጊዜ ነው።

# እምነት ምንድን ነው?

# የእምነት ምንነት እና እድገት

"እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።"
(ዕብራውያን 11:1)




ዕብራውያን 11:1፣ 3 እና 6 ላይ ስለእምነት ሰፊ መግለጫ ተሰጥቶናል። እምነት ስለ እግዚአብሔር ያለንን አመለካከት የሚገልጽ ነው። በፈጣሪነቱና በታማኝነቱ እርግጠኞች እንድንሆን ይመራናል።

የእግዚአብሔርን መልስ ስንጠባበቅ ሳለን ተስፋ እንዳንቆርጥ በቀሪው የምዕራፉ ክፍል ላይ ጳውሎስ ለእኛ አርአያዎችና መበረታቻዎች እንዲሆኑን የአያሌ አባቶችና እናቶችን እምነት ገልፆልናል።

ከዚህ ቀደም እንዳየነው ሁላችንም ተመሳሳይ የእምነት ደረጃ የለንም። ጥቂትም ቢሆን ብዙ ያለንን እምነት ማሳደግ የምንችለው እንዴት ነው?




ምንም ያህል አናሳ ቢሆን እምነትን ማጎልበት (ማቴ 17:20)



መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት (ሮሜ 10:17)



እግዚአብሔር እንዲያሳድግልን መለመን (ሉቃ 17:5)



ለጥርጣሬ ቦታን አለመስጠት (ማር 9:23-24)



እምነታችንን በሌላ ሰው እምነት ላይ አለመመስረት (ማቴ 25:8)



ለመንፈስ ቅዱስ መታዘዝ (ገላ 5:22)



እምነትን በየዕለቱ መለማመድ (2 ቆሮ 5:7)

# የኢየሱስ እምነት

"የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው።" (ራዕይ 14:12)



ለኢየሱስ ዳግም መመለስ ቅርብ የሆንን የታመንነው የምንለየው በምንጠብቃቸው (ማለትም በምንታዘዛቸው ወይም በምንይዛቸው) ሁለት ነገሮች ነው። እነርሱም ትዕዛዛቱና የኢየሱስ እምነት ናቸው (ራዕ 14:12)።

ሕጉ ወይም ትዕዛዛቱ እና ወንጌል ወይም እምነት የተሳሰሩ ናቸው።ያለ እምነት መታዘዝ አይቻልም፤ ያለመታዘዝም ማመን አይቻልም። ነገር ግን "የኢየሱስ እምነት" ማለት ምን ማለት ነው?

- ለኢየሱስ እና ለቃሉ ታዛዥ መሆን
- ከኢየሱስ ጋር በየዕለቱ ሕብረት ማድረግ
- ኢየሱስን የሕይወት ማዕከል ማድረግ
- እንደ እምነታችን አኗያ መኖር
- እምነታችንን በኢየሱስ ላይ መመስረት
- ኢየሱስን በሕይወታችን ማንጸባረቅ
- የእርሱን የጸጋ ስጦታ መቀበል



በኢየሱስ በማመን እንጸድቃለን (ሮሜ 5:1)፣ እንቀደሳለን (የሐዋ 26:18) እናም የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን (ዮሐ 1:12)።

“እንግዲህ በእያንዳንዱ እርምጃ ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመራችሁ ጌታ ኢየሱስን እመኑት። እጃችሁ በእጁ ውስጥ እንዳለ እርግጠኞች መሆን ስለምትችሉ ወደ ፊት በምትራመዱበት እያንዳንዱ እርምጃ እርግጠኝነትንና ብርታትን ልትቀበሉ ትችላላችሁ። “እየሮጣችሁ የማይደክማችሁ” እና “እየተጓዛችሁ የማትታክቱ” ትሆናላችሁ ምክንያቱም እጃችሁ በክርስቶስ እጅ እንዲያዝ በእምነት ማድረግ ስለምትችሉ ነው። በተስፋ መቁረጥ ውስጥ አትሰጥሙም ምክንያቱም ጌታን እያወቃችሁትና በእርሱ እየታመናችሁ ስትከተሉት በእርሱ ሙሉ በሙሉ የሚታመኑትን መቼም ቢሆን የማይረሳው እርሱ የእናንተ የሁልጊዜ ረድኤት እንደሆነ እርግጠኞች ስለምትሆኑ ነው።”

EGW (Our Father Cares, October 27)